አፋር ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት
የርዕሰ መስተዳድር ጽ/ቤት

Afar National Regional State Office
of the President



Qafar Agattinoh Rakaayih Doolatak
Rakaakay Xintoh Abbah Kutbeh Buxa



ቁጥር 2151-01
Ref.No.

ቀን 13/01/09
Date

በትግራይ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት

- ለርዕሰ መስተዳድር ፅ/ቤት

መቐለ፣

በሀገራችን ኢትዮጵያ እየተካሄደ ያለው የልማት ሂደት ያስቀናቸው የጠባብነትና የትምክህተኝነት አስተሳሰብና አመለካከት የተሸከሙ ፀረ-ልማት ኃይሎች በሀገራችን በአንዳንድ ክልሎች በተለይ በአማራ ክልል በፈጠሩት ሁከት ከ6000 በላይ የሚሆኑ ንጹሃን የትግራይ ክልል ተወላጆች ከቤት ንብረታቸው በመፈናቀላቸው የክልላችን ህዝብና መንግስት ሂደቱን ፀረ-ዲሞክራስና በሀገራችን እየተካሄደ ያለውን የልማት እንቅስቃሴ ለማደናቀፍ ሆን ተብሎ የተፈፀመ ድርጊት መሆኑን በጥሞና አይቶ አውግዞታል። በነዚህ ንፁሃን ዜጎች ላይ የደረሰው በደል በነሱ ብቻ ያነጣጠረ ብቻ ሳይሆን በመላእ የኢትዮጵያ ብሄር ብሄረ ሰቦችና ህዝቦች የተቃጣ ኣደጋ መሆኑን ኣስምሮበታል።

በመሆኑም የአፋር ህዝብና የትግራይ ህዝብ ባለፉት ዘመናት የኢትዮጵያ ብሄር ብሔረሰቦች መብት ለማስከበርና ሀገራችን የለማችና ያደገች እንድትሆን አስከፊውን ፊውዳሊዝምና ወታደራዊ ስርዓት ለመገርሰስ ያሳዩትን የማይረሳ የትግል አጋርነት የ2ቱን ክልል ህዝብ ባኣሁኑ ጊዜ ወደ ልማትና የመደጋገፍ ትስስር ኣሸጋግሮት ይገኛል። ለወደፊቱም በ2ቱ ክልል ህዝብ፣መንግስተና ገዥ ፓርቲዎች (በህውሀትና አብዴፓ) ያለውን ግንኙነት እየተጠናከረ የሚቀጥል መሆኑን በማስመር፤ የክልላችን ህዝብና መንግስት ወገን ለወገን በሚል መርህ የክልሉ መንግስት፣ ወረዳዎችና የልማት ድርጅቶች በየአቅማቸው ለተፈናቀሉ ወገኖቻችን ማቋቋሚያ የሚሆን ብር **10,266,000.00 /አስር ሚሊዬን ሁለት መቶ ስድሣ ስድስት ሺህ ብር/** የለገስን ሲሆን፣ ይህንን ድጋፍ ለማድረስ፣አጋርነታችንን ለማሳየትና በፀረ ህዝቦች ያለንን ተቃውሞ ለመግለፅ በህዝብ የተመረጡ የሀገር ሽማግሌዎችና የመንግስት ተወካዮች የላክን መሆኑ እየገለፅን፣ በቀጣይም የአፋር ክልል ህዝብና መንግስት እንደወትሮው ኮጎናችሁና ከመላው የኢትዮጵያ ህዝቦች ጎን ቆሞው የሀገራችን ልማትና ሰላም ዘላቂ ለማድረግ ፀረ ትምክህትና ጠባብነት ጠንክረን የምንታገል መሆኑን እናረጋግጣለን።

// ከሠላምታ ጋር //

ስዩም አወል አይዳሂስ
ርዕሰ መስተዳድር

ግጭባጭ፣

- በትግራይ ክልል ግብርናና እርሻ ልማት ቢሮ
  የአደጋ መከላከልና ዝግጁነት ጊዜያዊ ኮሚቴ

መቐለ፣

ስልክ ☎ 033 666 00 58
033 666 00 56
033 666 01 11

ፖ.ሳ.ቁ. 15
P.O.Box.

ፋክስ 033 666 03 82
Fax 033 666 03 91

ሠመራ
SEMERA

መልሱን በሚፅፉልን ጊዜ እባክዎን የኛን ደብዳቤ ቁጥር ይጥቀሱልን።

በአማራ ክልል ለተፈጠረው ችግር ከቤት ንብረታቸው ለተፈናቀሉት የትግራይ ክልል ተወላጆች ማቋቋሚያ ከክልሉ መንግስት፣ከ17 ወረዳዎች እና ከልማት ድርጅቶች የተሠበሰበ ገንዘብ የሚያሳይ ሠንጠረዥ

| ተ.ቁ | የወረዳ ሥም Daqara Magala | ቃል የተገባ ገንዘብ መጠን | | ምርመራ |
|---|---|---|---|---|
| | | ብር | ሣ | |
| 1 | አይሣኢታ (Aysaqiita Daqara) | 100,000 | 00 | |
| 2 | ሚሌ (Millê Daqara) | 100,000 | 00 | |
| 3 | ዱብቲ (Dubtê Daqara) | 100,000 | 00 | |
| 4 | አፋምቦ (AfambÔ Daqara) | 60,000 | 00 | |
| 5 | አብዓላ (Abqaala Daqara) | 100,000 | 00 | |
| 6 | መጋሌ (Magaale Daqara) | 126,000 | 00 | |
| 7 | ዳሎል (Xaalol Daqara) | 100,000 | 00 | |
| 8 | ኮነባ (Konnabi Daqara) | 100,000 | 00 | |
| 9 | በራህሌ (Baracle Daqara) | 100,000 | 00 | |
| 10 | እረብቲ (Erebti Daqara) | 100,000 | 00 | |
| 11 | አፍዴራ (Afxeera Daqara) | 100,000 | 00 | |
| 12 | አሚበራ (Qammibari Daqara) | 100,000 | 00 | |
| 13 | ገዋኔ (Gawwaani Daqara) | 100,000 | 00 | |
| 14 | ዳሊፋጌ (Xaale faageh Daqara) | 100,000 | 00 | |
| 15 | ተላላክ (Talaalák Daqara) | 100,000 | 00 | |
| 16 | ሃደለኤላ (Caxxale Qeelih Daqara) | 100,000 | 00 | |
| 17 | ጎሊና (Goolinâ Daqara) | 80,000 | 00 | |
| | ንዑስ ድምር | 1,666,000 | 00 | |
| 18 | ከክልሉ መንግስት ጥቅል በጀት | 8,000,000 | 00 | |
| 19 | ከአፋር ውሃ ሥራዎች ድርጅት | 400,000 | 00 | |
| 20 | ከአፋር ዲዛይንና ቁጥጥር ድርጅት | 200,000 | 00 | |
| | ጠቅላላ ድምር | 10,266,000 | 00 | |